# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሰኔ 26 ቀን 2005 ዓ.ም.

## የ2005 ዓም የሰሜን አሜሪካ የኢሕአፓ አባላት ኮንፈረንስ

ከሰኔ 24 እስከ ሰኔ 25 ቀናት 2005 ዓም በሰሜን አሜሪካ በቨርጂኒያ ግዛት የተካሄደው የሰሜን አሜሪካ አባላት ኮንፈረንስ÷በተሳካ ሁኔታ ተከናውኗል፡፡ ከተለያዩ የአሜሪካና የካናዳ ግዛቶች የተሰባሰቡ የኢሕአፓ አባላት ተወካዮችና የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባላት ተሳትፈዋል፡፡

ይህ ኮንፈረንስ÷ የሀገራችንን የፖለቲካ÷ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም የአካባቢያችንና የዓለም አቀፍ ነባራዊ ጉዳዮችን በጥልቀትና በስፋት ተወያይቶ ውሳኔዎችን አሳልፏል፡፡ በተለይም አገራችን አሁን የምትገኝበትን ለጎልውናዋ አስጊ በሆኑት አሳሳቢ ጉዳዮች ዙሪያ ረዘም ያለ ጊዜ በመውሰድ መርምሮ ከተወያየ በኋላ ÷ኮንፈረንሱ ፓርቲው ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው ነጥቦች ላይ ተነጋግሮ ውሳኔዎችን አስተላልፏል፡፡ የኮንፈረንሱ ተካፋዮች ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸውን ሁሉ ለመፈፀም ዝግጁ መሆናቸውን በድጋሚ አረጋግጠዋል ፡፡ የፓርቲ አባላት–አካላት ውህደት÷ለፓርቲው ጥንካሬና ለትግሉ መገስገስ ወሳኝ መሆኑን በማመን÷ የፓርቲውን ሕግና ደንብ አክብሮ መታገል መሠረት መሆኑን ተገንዝቧል፡፡

ኮንፈረንሱ÷በአለፈው ዓመት የተካሄደው አምስተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎችና የተግባር ዕቅዶች በሥራ መተርጎም እንዳለባቸው አስረግጧል፡፡

ለአለፉት ሁለት የሥራ ዘመን ኃላፊነታቸውን በብቃት በመወጣት የተሰናበቱትን የሰሜን አሜሪካ አህጉራዊ ኮሚቴ አባላትን ከልብ በማመስገን÷ በቦታቸው በመተካት ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት የሚያገለግሉትን አዲስ የአህጉራዊ ኮሚቴ አባላትን መርጧል፡፡

በመጨረሻም ፓርቲው ከወያኔ ጋር ለሚያካሂደው የሞት–ሽረት ትግል÷ ኅብረተሰባችን የተለመደውን ሙሉ ድጋፉፍና ትብብሩን እንዲቀጥል ወገናዊ ጥሪዉን አስተላልፏል፡፡

ኢትዮጵያ አገራችን ለዘለዓለም ትኖራለች !

ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው !


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France